# መሬት የግል ሃብት? ገጠሩንም ለወያኔ እንዳናስረክብ!!!

ከትላንት ወዲያ በንጉሱ ዘመንና ትላንት በደርግ አገዛዝ ተከስተው በመቶ ሽ የሚቆጠሩ ዜጎችን ህይወት እየቀጠፉ ያለፉት ርሃቦች መሰረታዊ ምክንያታቸው ድርቅ ሳይሆን ፖለቲካዊ ነበር። በወቅቱ ሁለቱም መንግስታት በየተራቸው ይህንን ጥፋት በድርቅ አመካኝተው ከሃላፊነት ሊያመልጡ ሞክረዋል። ዛሬ መከረኛው የኢትዮጵያ ህዝብ በሃገራችን በደርግ ዘመን " የክፍለ ዘመኑ ርሃብ " ተብሎ ከተሰየመው አስከፊ የመከራ ዘመን የባሰ ሁኔታ ውስጥ እየወደቀ ይገኛል። መለስ ዜናዊ ራሳቸው ከፊታችን የተደቀነው አደጋ በስፋቱም ሆነ በክፋቱ ከደርጉ ዘመን የባሰ ይሆናል ብለው መግለጫ ሰጥተዋል። የዚህም የአዲስ ዙር የመከራ ዘመን ምክንያቱ ድርቅ ብቻ አይደለም። መሰረታዊው ምክንያት እንደትላንቱና እንደትላት ወዲያው የፖለቲካ ምክንያት ነው። ግን ደግሞ ፀረ ህዝቦች ምንጊዜም ቢሆን ከታሪክ አይማሩምና የወያኔ መንግስትም እንደቀደሙት መንግስታት ችግሩን በድርቅ ላይ ለመለላከክና ከሃላፊነት ለማምለጥ እየሞከረ ይታያል።

ባለፉት ከባድ የርሃብ ፈተና ወቅቶች እንደሆነው ሁሉ ዛሬም ለተከሰተው ርሃብ የሚሰጡት ምክንያቶች ከሁለት ተከፍለው ሊታይ ይችላሉ። በአንድ በኩል ፖሊሲ ነክ ቢሆኑም ቴክንካዊ ሊባሉ የሚችሉ ምክንያቶች አሉ። የመስኖ እርሻ አለመስፋፋት፤ የህዝብ ቁጥር መጨመር፤ ለገበሬው አስፈላጊ የሆኑትን ግብአቶች ማቅረብ አለመቻል፤ የማሳዎች ጥበት ወዘተ የመሳሰሉት ከዚህ የሚደመሩ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ በቀጥታ ፖለቲካዊ የሆኑ ምክንያቶች አሉ። እነዚህ ደግሞ ስልጣን በጨበጠው ሃይል የተተከሉትን የመሬት ስሪቶች የሚመለከቱ ናቸው። ትላንትም ዛሬም ህዝባችን ለአስከፊ ርሃብ የተዳረገው በነዚህ በሚተጋገዙ ርሃብ ፈልላይ ክስተቶች ነው። ዛሬም በሃገራችን ሰማይ ላይ ለሚያንዣብበው የአስከፊ ርሃብ አደጋ በወያኔዎች የተተከለው የመሬት ስሪት እንደተጠያቂ ሆኖ ቀርቦ ከየአቅጣጫው የመሰረታዊ ለውጥ ጥያቄ እየቀረበ ነው። ነገር ግን የስሪት ለውጥ ያስፈልጋል ይባላል እንጂ ምን አይነት ለውጥ ለሚለው ጥያቄ ሁሉም አንድ አይነት መልስ የለውም።

በአንድ በኩል በርካታ ተቃዋሚ ድርጅቶች መሬትን የግል ሃብት የሚያደርግና ለገበሬው መሬቱን የመሸጥና የመለወጥ " መብት " የሚያረጋግጥ መሰረታዊ ለውጥ ይጠይቃሉ። በዚህ አቋዋም የተሰለፉት እነሱ ብቻ አይደሉም። ባለፉት አስር አመታት በአለም አቀፍ ደረጃ የነፃ ገበያ መርህ አራማጆችና የነሱ አፈ ቀላጤ የሆኑት አለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋዋማት ለእንደዚህ አይነቱ ለውጥ የወያኔን መንግስት ሲወተውቱና ጫና ሊያደርጉበት ሲሞክሩ እንደነበረ የአደባባይ ምስጢር ነው። ዛሬ በተከሰተው ቀውስም በመጠቀም እንዲህ አይነት ለውጥ እንዲደረግ ጫና እያደረጉ ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ የመሬት ይዞታ ስሪት ለውጥ እንዲደረግ ጥሪ እያደረጉ ነገር ግን መሬት የግል ሃብት ሆኖ ለገበሬው መሬቱን የመሸጥና የመለወጥ መብት ይታወቅለት የሚለውን ሀሳብ ተቃውመው ገበሬው በሚያርሰው ማሳ ላይ ከመሸጥና መለወጥ በመለስ የይዞታ ዋስትና የሚያረጋግጥ ለውጥ እንዲደረግ የሚታገሉ ሌሎች የፖለቲካ ተቃዋሚዎችና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶች አሉ።

በመሃል ከሶስት ሳምንታት በፊት በዚህ ጥያቄ ዋና ባለጉዳይ የሆኑት ገበሬዎች ምን እንደሚያስቡ የሚጠቁም በኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ማህበር የተካሄደ አንድ ጥናት ይፋ ሆኗል። ከጋምቤላ በስተቀር በሙሉ በሃገሪቱ ግዛቶች በተካሄደው በዚህ ጥናት እንደሚታየው ከሆነ መሬት የግል ሃብት የሚለውን ሃሳብ የሚደግፉ ከገበሬው ሰላሳ ሁለት በመቶ ብቻ ናቸው። አርባ ስድስት ከመቶው መሬት የመንግስት የሚለውን ስርአት በግልፅ ይደግፋሉ። ይህ ጥናት ዛሬ የሃገራችን ገበሬዎች በእርግጥ ስለሚጨነቁበት ጉዳይም ሌላ የሚለው ቁም ነገር አለው። ዋናው ችግራው የመሸጥ የመለወጥ መብት መነፈጋቸው ሳይሆን በሚያርሱት ማሳ ላይ የይዞታ ዋስትና ማጣታቸው ነው። ከገበሬዎቹ ሰባ ስድስት በመቶ ዛሬ የሚያርሱት መሬት የዛሬ አምስት አመት የነሱ ሆኖ መቆየቱን እርግጠኛ አለመሆናቸውን ተናግረዋል።

በኛ ግምት ይህ የይዞታ ዋስትና ጥያቄ ቁልፍ ጥያቄ ነው እንላለን። ገበሬው ምርቱን አሳድጎ፤ ራሱም ቤተሰቡም ጠግበው በልተው፤ የተረፈውን ደግሞ ገበያ አውጥቶ በሚያገኘው ገንዘብ ለተመቻቸ ኑሮ አስፈላጊ የሚላቸውን ቁሳቁሶች

ነው። በዚህ ወቅታዊ የሹምሽር አሰራር ንጉሱ የሚያተረማምሱት በዙሪያቸው የተኮለኮሉትን አፍኝ የማይሞሉ የገዥው መደብ ቀንደኛ አባላትን ብቻ ስለነበረ በህብረተሰቡ ላይ እምብዛም የሚያስከትለው ክፉም በጎም ለውጥ አልነበረውም። የወያኔ አካሄድ ግን አላማው ምንም እንኳዋን የፖለቲካ ቁጥጥር ቢሆንም ውጤቱ በደርዘን ሚልዮን የሚቆጠሩ የገበሬ ቤተሰቦችን ኑሮ በእንጥልጥል የሚይዝና ከአመት አመት ሳያደላድል በአንድ እግር አቁሞ የሚያስቀር ዘግናኝና ፀረ ልማት ፖሊሲ ነው።

የዚህ አሰራር ጨርሶ መሰረዝና የይዞታ መብት ሙሉ በሙሉ መረጋገጥ ለአራሹም ሆነ ለሃገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት እንደዚሁም በፖለቲካው መስክ ለዴሞክራሲ መስፈን ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ አይን በሚያወጣ መልክ ግልፅ ነው። የገበሬውን የማምረት ወኔ ያሳድጋል። ጉልበቱንም ሆነ ያለችውን ገንዘብ አፍስሶ ማሳውን እንዲንከባከብ፤ በመስኖ እንዲያርስ፤ ዛፍ እንዲተክል ያበረታታዋል። በፖለቲካው መስክም ገበሬው ከወያኔ አፉኝ ቁጥጥር ተላቆ ነፃ ምርጫ የሚሉት ሂደት በሃገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ትርጉም ይኖረዋል። በነዚህ ምክንያቶች የተነሳ ጥያቄው የዚያኑ ያህል ለወያኔዎችም የሞት ሽረት ጥያቄ ነው። ይህንን ለውጥ መቀበል ማለት በገበሬው ላይ ያላቸው የፖለቲካ ቁጥጥር ከእጃቸው እንዲያፈተልክ መፍቀድ ማለት ነው።

ዛሬ በተከሰተው ቀውስ ይህ ስሪት ከየአቅጣጫው እየተዋከበ ባለበት ወቅት የወያኔ መንግስት ለውጥ ለማምጣት እየተገደደ ቢሆንም ይህንን ለገበሬው የተሟላ የይዞታ ዋስትና የሚያረጋግጥ ለውጥ ያደርጋል ማለት ጨርሶ የዋህነት ነው። ከዚህ ይልቅ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ " መሬት የግል ሃብት " የሚለውን ሃሳብ በመደገፍ ለገበሬው የመሸጥና የመለወጥ " መብት " ሽንጡን ገትሮ የሚሙዋገትበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ምንም መጠራጠር አይቻልም።

እስካሁን ድረስ እንደታዘብነው ከሆነ ይህ መንግስት ከአሳዳሪዎቹ ባእዳንና የነፃ ገበያ ተብየው እኮኖሚ አራማጅ የፋይናንስ ተቋዋማት በሚደረግበት ጫና ከመዋቅር ማስተካከያ እስከ ፕራይቤታይዜሽን ያሉትን የነፃ ገበያ ለውጦች በሙሉ ተቀብሎ ሃገሪቱን ሲያተራምስና ህዝባችንን ከእለት እለት ለባሰ ድህነትና ማጣት ሲዳርግ የቆየ መንግስት ነው። ነገር ግን ደግሞ እነዚህን የነፃ ገበያ ለውጦች በተቀበለ ቁጥር ሁኔታዎችን ለወያኔ መሪዎችና በእነሱ ዙሪያ እየተበጀ ላለው አዲስ የደራሽ ከበርቴዎች መደብ ሁኔታውን እያመቻቸ እንደሆነና ዛሬ ከገጠሩ ውጭ ያለውን የግል የእኮኖሚ ዘርፍ ህገ ወጥ በሆኑ የፓርቲ ኩባንያዎች አማካኝነት መዳፉ ውስጥ እያስገባ እንደሆነ ሁላችንም የምናውቀው ነው። እስከዛሬ ድረስ የግል ኢኮኖሚውን መስክ መዳፋቸው ውስጥ ያስገቡት ወያኔዎችና ደጋፊዎቻቸው በገጠሩ የሚጠየቁትን የፕራይቤታይዜሽን ሂደት ያልተቀበሉት " ነፃ ገበያ " በአርሶ አደሩ አለም ቢገባ በሚፈጠረው የገበያ ግርግር ድሃውን ገበሬ ለጅብ እየዳረጉ ሊያግበሰብሱ የሚችሉትን ጥቅም አጥተውት አይደለም። በዚህ የለውጥ ሂደት ሳቢያ ሌት ተቀን በሚወተውቱዋቸው ባእዳን አሳዳሪዎቻቸው ፊትም " ይኸው በጠየቃችሁት መሰረት ነፃ ገበያ በገጠሪቱ ኢትዮጵያም ተፈቀደ" ቢሉ የሚያገኙትን ቅባሎት በቀላሉ ቆጥረውት አይደለም። እስካሁን ድረስ ይህንን አይነቱን ለውጥ ያልተቀበሉት አሁን የተከሉት የወቅታዊ የይዞታ ብወዛ ስርአት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሲያረጋግጥላቸው የቆየው የፖለቲካ ቁጥጥር ስለ በለጠባቸው ብቻ ነው። የግድ ለውጥ ይደረግ ከተባለ ያጡትን የፖለቲካ ቁጥጥር በኢኮኖሚ ቁጥጥር አካክሶ እዚያው በዚያው ደግሞ በሚልዮን በሚቆጠሩ በሃገራችን ገበሬዎች መቃብር ላይ ለመክበር ሰፊ አጋጣሚ ለሚከፍትላቸው የግል ሃብት አማራጭ ይሟገታሉ።

እዚህ ላይ ግልፅ መሆን ያለበት አንድ ነገር አለ። ለገበሬው የመሸጥና የመለወጥ " መብት " የሚታገሉ ወገኖች ደግመው ደጋግመው የሚያነሱት አንድ መከራከሪያ ይህ መብት ስለታወቀ ገበሬው የግድ መሬቱን ይሸጣል ማለት አይደለም የሚለው አጉል መከራከሪያ ነው። ከፍ ብለን የጠቀስነው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች ማህበር ጥናትም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ይመስላል። እንደ ጥናቱ ግኝት ከሆነ ከገበሬዎቹ ዘጠና ከመቶ ያህሉ ይህ መብት ቢታወቅላቸው እንኳዋን መሬታቸውን ለመሸጥ " እንደማይፈልጉ " አስታውቀዋል። እውነታቸውን ነው አይፈልጉም። ነገር ግን ጥያቄው የመፈለግ ወይም ያለ መፈለግ ጥያቄ አይደለም። ለችግር ሲዳረግና መግቢያ መውጫ ሲጠፋው በማዳበሪያ ወይም በሌላ እዳ ሲያዝ ገበሬው ሳይወድ አርሶ የሚያበላውን በሬውን ለመሸጥ ሲገደድ፤ የሚያደርገው ሲያጣ ሌላው ቀርቶ የቤቱን የቆርቆሮ ጣራ እየነቀለ ሲሸጥ ሰምኑን እንኳዋን ከሚሰራጩ ዘገባዎች እየታዘብን ነው። ሃገራችን

ስራሱም ለቤተሰቡም መሸመት እንዲችል፤ ከዚህም አልፎ የተለያዩ የልማት ተቋዋሞችን ዘርግቶ ኑሮውን እንዲያሻሽል ከፈለገ የያዛትን ማሳ ምርተኛነት ለማሳደግ በመስኖ ለማረስ፤ ዛፍ ለመትከል ወዘተ ጉልበቱንም ገንዘቡንም ማፍሰስ አለበት። ተንከባክቦ የያዛትና ጉልበትና የሌለውን ገንዘብ አፍስሶ ምርታማ ያደረጋትን ማሳ ነገ ለሌላ ታስረክባለህ ወይም ልታስረክብ ትችላለህ ከተባለ የማምረት ቅስሙ ይሰበራል። ዋና ባለ ጉዳይ የሆኑት በደርዘን ሚልዮን የሚቆጠሩ ገበሬዎች በዚህ መልክ የማምረት ቅስማቸው እስከተሰበረ ድረስ ከሃገራችን ርሃብን እናጠፋለን ማለት ዘበት ነው። በደርግ ዘመን "ታጥቦ ጭቃ" የሆንነውና ለስመ ጥፋው "የክፍለ ዘመኑ ርሃብ" የተጋለጥነው ደርግ የኢትዮጵያ ገበሬዎችን ዴሞክራሲያዊ አብዮት ቀልብሶ የማምረት ቅስማቸውን ስለሰበረ እንጂ መሬት የመንግስት ስለሆነ አልነበረም። ዛሬም እንደገና ከክፍለ ዘመኑ ርሃብ ሶስት እጥፍ ሊከፋና ሊሰፋ ይችላል ተብሎ ለሚፈራው ርሃብ በመጋለጥ ላይ ያለነው ገበሬው ድሮውንም ቢሆን የማይጨነቅበትን የመሸጥና መለወጥ መብት ስለተነፈገ ሳይሆን ማሳውን " ዛሬ የኔ፤ ነገ የልጆቼ "ብሎ እንዳይንከባከባትና ተረጋግቶ እንዳያርስ የፍጥኝ አስሮ የያዘ የመሬት ፖሊሲ ስለተተከለበት ነው።

በመሰረቱ መሬትን የህዝብ ያደረገው የመሬት ስሪት የኢትዮጵያ ገበሬዎችና መሬት ላራሹ ብሎ ተነስቶ ከጎናቸው ተሰልፎ የተሰዋ የአንድ ትውልድ የትግልና የመስዋእትነት ፍሬ ነበር። መሬት ድሃው አራሽ እጅ ስለገባ ምርት ይንኮታኮታል፤ ያልታየ ያልተሰማ ርሃብ ሃገሪቱን ያላብሳል ተብሎ ሲፈራ በመጀመሪያዎች የአብዮት አመታት ገበሬው ይህንን ድሉን ሊነጥቁት በመሳሪያም ጭምር ከሚፈታተኑት ሃይሎች ጋር እየተፋለመም ቢሆን ምርቱን አሳደገ። የዚህ የምርት ማደግ ውጤት ገበሬውና ቤተሰቡ የምግብ ፍጆታቸውን በአማካኝ በአስራስስት በመቶ ጨምረው ጠግበው ማደራቸው ብቻ አልነበረም። ከእንግዲህ የላቡ ፍሬ ባለቤት የሆነው ገበሬ በትርፍ ምርቱ ትምህርት ቤቶች፤ የጤና ጣቢያዎች፤ መጋቢ መንገዶች፤ የውሃ ጉድጉዋዶች፤ ወፍጮ ቤቶችና ሌሎች ልዩ ልዩ የልማት ተቋዋሞችን ለመዘርጋት አልሞ በዚህ የአዲስ ህይወት ጎዳና ተሰማራ። በአብዮት ደጋፊነት የማይጠረጠረው ዋሽንግተን ፖስት የተባለው ጋዜጣ ይህንን ክስተት " የኢትዮጵያ ተአምር" ብሎ ጠራው። ተአምሩ ግን ብዙ አልቆየም።

ከእንግዲህ የበይ ተመልካች መሆኑ ያከተመው ገበሬ ከራሱ ተርፎት ገበያ ለሚያወጣው እህል ተገቢ ዋጋ ጠየቀ። እዚህ ላይ ዝርዝር በማንገባባቸው በርካታ ምክንያቶች ከተሞች በበኩላቸው ምርታቸውን አሳድገውና አሰበጣጥረው የገበሬውን ፍላጎት ሊያሟሉለት አልቻሉም። በዚህ ሁኔታ ገበሬው ለምርቱ ተመጣጣኝ ዋጋ ባለማግኘቱ እህሉን ገበያ ከማውጣት ይልቅ ጎተራ መክተት ጀመረ። የደርግ መንግስት ለዚህ ችግር ያገኘው መፍትሄ በእህል ቦርድ አማካኝነት እያንዳንዱ አራሽ ደርግ ራሱ በሚተምነው አልባሌ ዋጋ እህል ለመንግስት ጎተራ እንዲያስገባ ኮታ መጣል ነበር። ገበሬው ምርቱን እንዳይቀማ ዴሞክራሲያዊ በሆነ ዘዴ መርጦ "የኔ" በሚላቸው መሪዎቹ አማካኝነት ከደርግ መንግስት ጋር ከባድ ፍልሚያ ውስጥ ገባ። በ1970 እና በ1971 አ.ም. በሃገራችን ገጠሮች በሁለቱ ሃይሎች መሃከል ሰፊና እልህ አስጨራሽ ትግል ተካሄደ። በዚህ ትግል ሳቢያ በሃገራችን ገጠሮች በተካሄደው ጭፍጨፋ ከገበሬ ማህበራት ከሩብ በላይ ጨርሰው ፈርሰው ከሃያ አምስት ሽህ አስራ ዘጠኝ ሽህ ብቻ ቀሩ። ቀኝ መንገደኛ፤ ጠባብ ብሄርተኛ፤ ኩላክ፤ ፀረ አብዮት እየተባሉ ከሁለት መቶ አምሳ ሽህ በላይ የሚሆኑ የገበሬ ማህበራት መሪዎች ተሸረው፤ ታስረው፤ በቀይ ሽብር ተቀጥፈውና ተሰደው የገጠሩ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ተቀለበሰ። በሃገችን ገበሬዎች የልማትና የተሻለ ኑሮ ህልም መቃብር ላይ ፀረ ህዝቡ ደርግ የህብረት እርሻና መንደር ምስረታ በሚሉ ፈሊጦች ምርቱንም መሬቱንም ከአርሶ አደሩ ቀምቶ ገጠሩን አተረማመሰው። ተከትሎ የተከሰተው ስመ ጥፋው " የክፍለ ዘመኑ ርሃብ" ዋና ምክንያት በደርዘን ሚልዮን የሚቆጠሩ የሃገራችን ገበሬዎች የማምረት ቅስም በዚህ መልክ በመሰበሩ ነበር።

ዛሬስ? ዛሬም ቢሆን በወያኔዎች የተተከለው ስሪት የገበሬውን የማረት ቅስም የሚሰብር ስሪት ነው። ገበሬው በሰማይ ጠቀስ ግብር፤ በመዋጮ፤ በማዳበሪያ እዳና በሌሎች በተለያዩ ምክንያቶች ከሚገባው በላይ የላቡን ፍሬ ይቀማል። በሚያርሰው መሬት ላይ ምንም አይነት የይዞታ ዋስትና የለውም። ያለው ወቅታዊ የይዞታ ብወዛ ስርአት ስለሆነ ገበሬው በየወቅቱ እየተገመገመ የወያኔ ደጋፊ ደግ ደጉን መሬት ሲያገኝ በተቃዋሚነት የሚታወቀው ወይም የሚጠረጠረው ደግሞ ከያዘው ማሳ ተነቅሎ አልባሌ መሬት ላይ ይጣላል።

ይህ አሰራር በንጉሱ ዘመን ይካሄድ የነበረው ሹም ሽር ከተባለው የፖለቲካ ቁጥጥር ዘይቤ ጋር የሚመሳሰል

ባንሰራፋው ድህነት፤ በሚልዮን የሚቆጠሩ ገበሬ ቤተሰቦች በኑሮ ጠርዝ ላይ ተንጠልጥለው ባሉበት ሁኔታ፤ በኢኮኖሚው መስክ በሙሰኝነት የተዘፈቀና በፖለቲካው መስክ አፈናና የዘፈቀደ አገዛዝ በሰፈኑበት ስርአት የትኛው መብቱ እንደተረጋገጠለት ነው ገበሬው "መሬትህን የመሸጥ የመለወጥ መብት ታውቆልሃል" ሊባል የሚችለው? በዚህ ሁኔታ ለሃገራችን ድሃ ገበሬዎች የሚረጋገጠው ሌላ ምንም ነገር ሳይሆን የመሸጥ ግዴታ ነው። መብት የሚሉ ነገር ካነሳን የሚረጋገጠው ለወያኔዎችና ምናልባትም የባእድ ካፒታሊስቶችን ሊያካትት ለሚችለው የደጋፊዎቻው ሰፈር የሚታወቀው መሬት የመግዛት መብት ብቻ ነው።

መሬት የግል ሃብት የሚሉትን ሃሳብ የምንቃወምበት ብዙ መሰረታዊ ምክንያቶች አሉ። ይህ ወደፊት ዴሞክራሲ በሰፈነበትና ዋናዎቹ ባለጉዳዮች የሆኑት የሃገራችን ገበሬዎችም በሰፊው በሚሳተፉበት ውይይት እልባት የሚያገኝ ጉዳይ ነው። ዛሬ የዴሞክራት ተቃዋሚዎች ዋና ተግባር መሬት የግል ሃብት ይሁን በሚለው ቅስቀሳ ተሰማርተው በግርግር እንዲህ አይነቱ "መመለሻ የሌለው" የስርአት ለውጥ ለወያኔዎች በወያኔዎች እንዲወሰድ ማራገብ አይደለም። ከዚህ ይልቅ እዛው በዛው ገበሬውን ከወያኔ የፖለቲካ ቁጥጥር ስር አላቆ ለሃቀኛ ዴሞክራሲ በር ለሚከፍትለትና በኢኮኖሚውም መስክ በተረጋጋ መንፈስ ማሳውን እየተንከባከበ ምርቱን ሊያሳድግ ለሚችልበት የተሙዋላ የይዞታ ዋስትና መብት ከጎኑ ቆሞ መታገል ያስፈልጋል። ይህንን የምንለው መሬት የግል ሃብት የሚለው ፖሊሲ ለሃገራችን እድገት የተሻለ አማራጭ ይሆናል በሚል እምነት ለዚህ አላማ የሚታገሉ ወገኖች እምነታቸውን ትተው በኛ አቋዋም ይሰለፉ ለማለት አይደለም። ዛሬ በሃገራችን ባለው ሁኔታ ለዚህ ፖሊሲ ስንታገል በነፃ ገበያ መርህ ስም እንደከተማው የኢኮኖሚ ዘርፍ ገጠሩንም ለወያኔ ሙሰኛና ደራሽ ከበርቴዎች አስረክበን ነገሩ ሁሉ ሰዶ ማሳደድ እንዳይሆንብን ለጊዜው በጥንቃቄ እንራመድ ለማለት ብቻ ነው።